

**SPECIAL EDUCATION RESOURCE HUB:**
**What Families & Students Need to Know this Year**

# MY CHILD IS CHANGING SCHOOLS OR STARTING TO THINK ABOUT LIFE AFTER HIGH SCHOOL

PAGE


**2** ትምህርት ቤቶች መቀየር፣ ሽግግር

1. በዚህ አመት ትምህርት ቤት የሚቀይረውን ልጄን እንዴት መርዳት እችላለሁ?
2. ልጄ በዚህ አመት አዲስ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ከሆነ፣ልጄ ምን እንደሚያስፈልገው አዲሱ ትምህርት ቤት እንዴት ያውቃል?
3. እኔ ስለልጄ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ስላለው የወደፊ ህይወት ማሰብ ጀምሪያለሁ። ትምህርት ቤቱ ልጄ ቀጥሎ ስለሚመጣው ነገር እንዲዘጋጅ እንዴት ሊረዷቸው ይችላሉ?

**3** የልጅዎ መብቶች

4. ልጄ የአካል ጉድለት እንዳለበት በምርመራ ተረጋግጧል። ከነሱ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፎችን እጠብቃለሁ?
5. ለልጄ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አስተማማኝ ካልሆነ፣ ትምህርት ቤቱ ቤት ውስጥ እንዲማሩ ሊያግዛቸው ይችላል?

**4** በዚህ የትምህርት አመት ምን መጠበቅ እንደሚገባ

6. COVID-19 ባለበት ሁኔታ፣ በመጪው አመት ከልጄ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፍ እጠብቃለሁ?
7. የኔ ልጅ በዚህ ጳደይ የትምህርት እድገቱን አጥቶ ይሆናል ብየ እሰጋለሁ። ልጄ እንዲተካከል ለማገዝ ትምህርት ቤቱ ምን ሊያደርግ ይችላል?
8. ልጄ የህዝብ ባልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት ተመድቧል። የነሱ ትምህርት ቤት ስለበጋ ያላቸውን እቅድ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

**5** ለእርዳታ ማንን ማግኘት እንደሚገባ

9. በትምህርት ቤት ውስጥ እኔ እና ልጄ ልናገኝ የሚገባን አገልግሎቶች እና ድጋፎችን አስመልክቶ እንዴት መከራከር እችላለሁ?
10. የልጄ ፍላጎቶች እንደተቀየሩ ወይም ትምህርታቸው ወይም ክህሎታቸው እንደቀነሰ ካመንኩ ማንን ማግኘት አለብኝ?
11. እኔ እና ልጄ ከትምህርት ቤቱ የሚያስፈልገንን ድጋፍ ካላገኘን የት መሄድ እችላለሁ?

**6** በዚህ አመት ልጅዎን እና ቤተሰብዎን መደገፍ

12. ልጄ ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እያገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቴን መጠየቅ ያለብኝ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?
13. ስለልጄ እድገት የት መማር እችላለሁ?
14. በዚህ የርቀት ትምህርት ወቅት ልጄን በተሻለ ሁኔታ ቤት ውስጥ እንዴት ልደግፈው እችላለሁ?
15. በዚህ ወቅት ጭንቀትን ለመቋቋም እና ለደህንነት ቤተሰቤ ምን ማድረግ ይችላል?

**7** ማጓጓዣ፣ የትምህርት ቤት ክትትል፣ስነምግባር፣የትምህርት ቤት ሪከርዶች

16. የትምህርት ቤት ህንጻዎች ከተከፈቱ፣ ልጄ አስተማማኝ የሆነ ትራንስፖርት ማግኘቱን እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?
17. ትምህርት ቨርቹዋል ከሆነ የትምህርት ቤት የመገኘት ክትትል እንዴት ይሰራል?
18. የልጄ ትምህርት ቤት በዚህ አመት የስነምግባር አያያዙ እንዴት ነው?
19. የልጄን የትምህርት ቤት ወይም የልዩ ትምህርት ሪከርዶች ቅጂን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?



# SPECIAL EDUCATION RESOURCE HUB:
## What Families & Students Need to Know this Year

## MY CHILD IS CHANGING SCHOOLS OR STARTING TO THINK ABOUT LIFE AFTER HIGH SCHOOL

## ትምህርት ቤቶች መቀየር፣ ሽግግር

### 1 በዚህ አመት ትምህርት ቤት የሚቀይረውን ልጄን እንዴት መርዳት እችላለሁ?

የልጅዎ አዲሱ ትምህርት ቤት ልጅዎን ለማስተማር እየተዘጋጀ ባለበት ሁኔታ፣ የሚከተሉት እርስዎ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ልዩ ተግባሮች ናቸው፣

ስለልጅዎ አዲሱ ትምህርት ቤት የበለጠ ማወቅ። መረጃ ለማግኘት የDC የትምህርት ቤት የሪፖርት ካርድ ጥሩ መነሻ ነው። በተጨማሪ፣ የህዝብ ያልሆኑ ትምህርት ቤት ፕሮፋይሎችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ።

የልጅዎን አስተማሪ እና የልዩ ትምህርት አስተባባሪን ማግኘት እና ያሎትን ማንኛውንም ጥያቄዎች መጠየቅ። የልጅዎ ትምህርት ቤት የሚገኙበትን መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ፣

- DC የህዝብ ትምህርት
- DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች
- የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች

ስለልጅዎ የሚያውቁትን ያጋሩ። ከሁሉም በተሻለ ልጅዎን የሚያውቁ በመሆኑ፣ የሚከተሉትን በማድረግ ማገዝ ይችላሉ፣

- የልጅዎን ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶችን መግለጽ
- በዚህ የጸደይ የርቀት ትምህርት ወቅት ውጤታማ እና ውጤታማ ያልሆኑ ተግባሮችን ማጋራት
- ልጅዎ ትምህርት ቤቶችን የሚቀይሩበትን ምክንያት ማጋራት

በተጨማሪ ልጅዎን በሚከተለው መንገድ መርዳት ይችላሉ፣

- ከትምህርት ቤት ስራ በተጨማሪ ልጅዎ ክህሎቶችን እና የተለመዱ ተግባሮችን እንዲያዳብር ማገዝ። ይህ በተለይ ልጅዎ ለመጀመርያ ጊዜ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመርያ ጊዜ በሚጀምሩበት ወቅት ጠቃሚ ነው።
- የአካል ጉድለት ካለባቸው ሌሎች ቤተሰቦች ጋር መገናኘት። ትምህርት ቤቶችን ሲቀይሩ ወይም በርቀት ትምህርት ጊዜ ልጃቸውን እንዴት እንደደገፉ ይጠይቋቸው። እንደ የመንግስት የልዩ ትምህርት የአማካሪ ፓነል (SAPSE) አይነት ቡድኖች ሌሎች ቤተሰቦችን ሊያገኙበት የሚችሉ ስብሰባዎች አሏቸው።
- ከተቻለ፣ልጅዎ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የቡድን ውይይቶች ላይ እንዲሳተፍ ያድርጉ።

### 2 ልጄ በዚህ አመት አዲስ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ከሆነ፣ልጄ ምን እንደሚያስፈልገው አዲሱ ትምህርት ቤት እንዴት ያውቃል?

የልጅዎ አዲሱ ትምህርት ቤት፣ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራማቸው (IEP) ላይ እንደተገለጸው ልጅዎ የሚያስፈልገውን ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች እና ድጋፎችን መስጠት አለባቸው።

የልጅዎ አዲሱ ትምህርት ቤት የልጅዎን IEP በመገምገም ይጀምራል። እነሱ በግምገማው ሂደት እና የልጅዎ IEP ላይ በሚደረጉ ማንኛውም የለውጥ ውሳኔዎች ላይ እርስዎ እንዲካተቱ ያደርጋሉ.። ይህ ልጅዎ በአዲሱ ትምህርት ቤት ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ መደረግ አለበት።

የልጅዎ አዲስ ትምህርት ቤት ልጅዎ በፊት ይማርበት ከነበረ ትምህርት ቤት ያሉ ሪከርዶች እና IEP ያገኛሉ። በተጨማሪ እነሱ የIEP ሲመረምሩ የልጅዎ የቀድሞ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን መረጃ ያያሉ። ይህ መረጃ የሚከተሉትን ይካትታል፣

- በIEP ያልተዳሰሱ ስፍራዎች ላይ የልጅዎ የአሁን ጊዜ አፈጻጸም
- እንደወላጅ ያሎት ስጋቶች
- ከልጅዎ የቀድሞ ትምህርት ቤት የIEP ግቦች እድገት ጋር የተያያዘ ዳታ

አዲሱ ትምህርት ቤትዎ የልጅዎ ሪከርዶች ይደርሰዋል፣ ነገር ግን እስኪላኩ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። ቅጂው ካሎት፣ በተቻለ ፍጥነት ቀደም ብለው ማቀድ እንዲጀምሩ የልጅዎን IEP ከአዲሱ ትምህርት ቤት ጋር ማጋራት ጠቃሚ ይሆናል።

አዲሱ ትምህርት ቤት የሚገኝበትን አድራሻ ከፈለጉ፣ እዚህ መፈለግ ይችላሉ፣

- DC የህዝብ ትምህርት
- DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች
- የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች

### 3 እኔ ስለልጄ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ስላለው የወደፊ ህይወት ማሰብ ጀምሪያለሁ። ትምህርት ቤቴ ልጄ ቀጥሎ ስለሚመጣው ነገር እንዲዘጋጅ እንዴት ሊረዷቸው ይችላሉ?

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ስላለው ህይወት ማሰብ አስጨናቂ ሊሆን ቢችልም፣ ትምህርት ቤትዎ የወደፊት ህይወታቸውን እንዲያቅዱ ልጅዎን ያግዛሉ።

ሂደቱ፣ ይህ ሂደት "የሽግግር እቅድ" ተብሎ ይጠራል። ይህ ልጅዎ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ምን እንድሚፈልጉ ማወቅ እና እንዴት እዚያ ላይ መድረስ እንደሚቻል መለየትን ያካትታል። በDC ውስጥ፣ ልጅዎ 14 አመት ሲሞላው መጀመር አለበት እና በየአመቱ መከለስ አለበት። ግቡ ልጅዎ እራሱን የቻለ ወጣት አዋቂ እንዲሆን ማስቻል እና እነሱ ኮሌጅ መግባት፣አንድ

የተወሰነ ሞያን መያዝ፣ ወይም ሌሎች ድጋፎችን ማግኘት እንደሚፈልጉ ለማየት ነው።

ቡድኑ፣ የሽግግር ቡድን ከእርስዎ እና ከልጅዎ ጋር ይሰራል። የሽግግር ቡድን ሊያካትት የሚችለው አስተማሪዎችን፣ ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞችን፣ እና የኤጀንሲ ወይም የማህበረሰብ ተወካዮችን ነው። በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤቱ የልጅዎ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ስላለው ግቦች እና እቅድ ለመወያየት ልጅዎ የIEP ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉ መጋበዝ አለባቸው። ልጅዎ ከድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽግግር እቅድ ላይ መሪ ሚና እንዲጫወቱ ይበረታታሉ።

እቅዱ፣ በአንድነት የተጻፈ "የሽግግር እቅድ" ታዘጋጃላቹ። ይህ እቅድ ከትምህርት ቤት በኋላ የልጅዎን ጥንካሬዎች፣ፍላጎቶች እና ግቦችን መሰረት ያደረገ ነው። ይህ እቅድ አንድ ጊዜ ከተጻፈ በኋላ፣ እርስዎን የሚያካትተው የልጅዎ የIEP ቡድን፣ በራሳቸው IEP ላይ ያሉትን ግቦች ያሻሽላሉ። እነዚህ አዲስ ግቦች ልጅዎ ትምህርት ቤት ባሉበ ወቅት ለሽግግር እንዲዘጋጅ እንዲረዱ የታቀዱ ናቸው።

ተጨማሪ ግብዓቶች፣

- የOSSE የሁለተኛ ጊዜ የሽግግር ሂደት መሳርያ
- የSchoolTalk ድረገጽ እና "ቀጥሎ የሚመጣው ምንድን ነው" ሰነድ
- በሽግግር ወቅት የDC አጋሮች

## የልጅዎ መብቶች

### 4 ልጄ የአካል ጉድለት እንዳለበት በምርመራ ተረጋግጧል። ከነሱ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፎችን እጠብቃለሁ?

ትምህርት ቤትዎ የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ሊያሟላ የሚችል በልዩ ሁኔታ የታቀደ ትምህርት ያለምንም ወጪ ለልጅዎ ይሰጣል። ይህ የሚከተለውን ያካትታል፣

- ልጅዎ በልዩ ሁኔታ የታቀደ ትምህርት ያገኛሉ። ፍላጎቶቻቸውን መሰረት በማድረግ፣ እነሱ በተጨማሪ ለንግግር ቴራፒ (ህክምና) ወይም የካውንስሊንግ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ወላጅ የሆኑትን እርስዎን ጨምሮ አስትማሪዎችን እና ሌሎችን የያዘ ቡድን፣ ተማሪው የሚያገኘውን አገልግሎቶች እና ድጋፍ ይወስናል።
- ይህን ትምህርት የመስጠት እቅድ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) መጻፍ አለበት።
- ትምህርት ቤትዎ በመላው የትምህርት አመት ሪፖርቶች ወይም ማሻሻያዎችን ይሰጠዎታል። በተጨማሪ ያሎትን ማናቸውም ስጋቶች መወያየት ይችላሉ።
- እርስዎ እንደወላጅነትዎ የልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ለመረዳት እና ለማገዝ እንዲረዳዎ የልጅዎ የIEP አካል የሆነ ስልጠና ሊያገኙ ይችላሉ።

የፌደራል ህግ የሆነው፣የአካል ጉድለት ያለባቸው ሰዎች የትምህርት ህግ (IDEA) "ነጻ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት " (FAPE በመባል በተጨማሪ የሚታወቀውን) መብትን፣የአካል ጉድለት ላለባቸው ልጆች ይጠብቃል። ይህ መብት ልጅዎ በ DCPS ትምህርት ቤት ወይም የDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት የተመዘገበ ቢሆንም፣ ወይም የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ቢሆንም ተፈጻሚ ነው።

በተጨማሪ IDEA፣ ልጅዎ FAPE ማግኘቱን ለማረጋገጥ "ስነስርዓታዊ ጥበቃዎች" ተብለው የሚታወቁ ሌሎች ብዙ መብቶችን ይጠብቃል። የOSSE ስነስርዓታዊ ጥበቃዎች ማስታወቂያ የእነዚህ መብቶች የበለጠ ዝርዝር ገለጻዎች አለው።

COVID-19 የልጅዎን መብቶች አይቀይርም። ልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ቨርቹዋል የሚማር ቢሆንም እነዚህ ተመሳሳይ ናቸው። ነገር ግን በዚህ አመት፣ ልዩ ትምህርት ለልጅዎ የተለየ አይነት እና የተለየ ስሜት ሊኖረው ይችላል። "በቀጣዩ አመት፣COVID-19 ባለበት ሁኔታ ከልጄ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፍ እጠብቃለሁ?"፣ የሚለው ጥያቄ ስለዚህ የበለጠ መረጃ ይሰጣል።

- ጥያቄዎች ካሉት፣ የልጅዎን አስተማሪ ወይም የልዩ ትምህርት አስተባባሪውን ያነጋግሩ

### 5 ለልጄ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አስተማማኝ ካልሆነ፣ ትምህርት ቤቴ ቤት ውስጥ እንዲማሩ ሊያግዛቸው ይችላል?

ልጅዎ ወደትምህርት ቤት መመለስ ባይችልም ሌሎች ተማሪዎች በአካል አገልግሎቶችን ለማግኘት እየተመለሱ ከሆነ፣ ትምህርት ቤትዎ ልዩ ትምህርትን መስጠት መቀጠል አለበት።

የትምህርት ቤት ህንጻዎች ከተዘጉ፣ ወይም የጤና ባልሞያዎች ወይም የልጅዎ ሀኪም ልጅዎ ቤት ውስጥ መቆየት እንዳለባቸው ከተናገሩ፣ የልጅዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ያግዛሉ።

የግል የቤት ውስጥ ትምህርት በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ሊሰጥ ይችላል፣ ከታች ያሉት የልጅዎ የ IEP ቡድን ግምት ውስጥ የሚከታቸው ጥቂት አማራጮች ናቸው። ይህ የሚከተለውን ሊያካትት ይችላል፣

- የስልክ ጥሪዎች
- የቤት ስራዎች
- ኢንተርኔትን መሰረት ያደረገ ትምህርቶች

የልጅዎ የIEP ቡድን የልጅዎን የቤት ውስጥ ትምህርት በማቀድ ላይ ከእርስዎ ጋር ይሰራል። ይህም  የቤተሰብዎን ጤና እና ደህንነት በማጣጣም፣በልጅዎ IEP የሚጠየቀውን በርቀት የትምህርት ሞዴል ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ ትምህርት ማግኘትን ያካትታል። ይህም ምናልባት ሁሉም ባይሆኑም፣ የተወሰኑ የልጅዎ የIEP አገልግሎቶች ልጅዎ ቤት ውስጥ በሚማርበት ጊዜም ሊሰጡ ይችላሉ ማለት ነው። በተጨማሪ ይህ የIEP አገልግሎቶች በፊት ከነበሩት የተለዩ ሊመስሉ ይችላሉ ማለት ነው። ለምሳሌ፣ ልጅዎ በቨርችዋል የሚከታተለውን የትምህርት ሰዓታት መሰረት በማድረግ፣ ልጅዎ በIEP ከሚፈለገው ልዩ የትምህርት ሰዓቶች ውስጥ የተወሰነውን ክፍል ብቻ ሊያገኙ ይችላል፣ ወይም ልጅዎ ከአቻዎቹ ጋር ባንድነት ከመሆን ይልቅ የንግግር እና የቋንቋ አገልግሎቶችን ብቻውን ከቴራፒስቱ ሊያገኝ ይችላል። እነዚህን አገልግሎቶች በዚህ የትምህርት አመት እንዴት ማስመለስ እንደሚቻል ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር መወያየት አለብዎ።

የIEP አካል የሆነው የቤት ውስጥ ትምህርት እንደ ቤት ውስጥ ማስተማር ተመሳሳይ እንዳልሆነ ያስታውሱ። በቤት ውስጥ የሚማሩ ልጆች በDC ትምህርት ቤታቸው እንደተመዘገቡ ነው። በቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ከDC ትምህርት ቤቶች ማንኛውም አይነት ልዩ ትምህርት ወይም አገልግሎቶችን አያገኙም።

ለበለጠ መረጃ፣ የ OSSE የልዩ ትምህርት እና COVID-19 መመርያን ይመልከቱ።

## በዚህ የትምህርት አመት ምን መጠበቅ እንደሚገባ

### 6 COVID-19 ባለበት ሁኔታ፣ በመጪው አመት ከልጄ ትምህርት ቤት ምን አይነት ድጋፍ እጠብቃለሁ?

ትምህርት ቤትዎ ለዚህ የትምህርት አመት እቅድ ላይ ጠንክሮ ሰርቷል። ከታች ያሉት እርስዎ እና ልጅዎ ከትምህርት ቤትዎ የሚጠብቋቸው ቁልፍ ነገሮችን ያካትታሉ። ጥያቄዎች ካሉት፣ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ።

1) ምንም እንኳን በአካል ትምህርት ባይኖርም፣ የርስዎ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርትን መስጠት መቀጠል አለባቸው። ይህ የቤተሰብዎን የጤና እና የደህንነት ፍላጎቶችን በማጣጣም በርቀት የትምህርት ሞዴል ሊሰጥ የሚችለውን፣በልጅዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም የሚጠየቀውን ልዩ ትምህርትን ማግኘት ያካትታል። ነገር ግን፣ በርቀት ትምህርት ወቅት የተወሰኑ ትምህርቶች እና አገልግሎቶች የተለዩ ሊመስሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

- የልጅዎን የአካል ጉድለት ለማጣጣም መማር የተወሰኑ ቨርቹዋል መንገዶችን ሊያካትት ይችላል።
- የአገልግሎት አቅራቢዎችን በስልክ ወይም በቪዲዮ ሊያገኟቸው ይችላሉ።
- ልጅዎ በቤት ውስጥ ስራ ለመስራት የሚያግዝ አዲስ ቴክኖሎጂ ሊያስፈልጋቸው ይችላል ("ደጋፊ ቴክኖሎጂ" ተብሎ ይጠራል)። ይህ ለርቀት ትምህርት አገልግሎት ላይ ከሚውለው መሳርያ የተለየ ነው እና ጽሁፍን የሚያስተልቅ ወይም ጮክ ብሎ ለማንበብ የሚያስችል ሶፍትዌርን ሊያካትት ይችላል።

ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር መስጠት ያልቻሉ አገልግሎቶችን በዚህ አመት እንዴት ማካካስ እንደሚቻል መወያየት ይችላሉ።

2) የእርስዎ ትምህርት ቤት፣ የልጅዎን IEP ለመመርመር እና ለማሻሻል እንደአስፈላጊነቱ ከእርስዎ ጋር አጋር መሆን አለባቸው። ለልጅዎ አስፈላጊ ከሆነ፣ ይህ ሂደት የልጅዎ ፍላጎቶች በምን መልኩ እንደተቀየሩ እና ልጅዎ በቤት ውስጥ ወይም ትምህርት ቤት ቢማሩ እንዲዚህ ፍላጎቶች እንዴት ሊሟሉ እንደሚችሉ ማየት አለበት። በተጨማሪ ልጅዎን ለመደገፍ እርስዎ እንደወላጅነትዎ የሚያስፈልግዎትን ስልጠና ማየት አለበት። ልጅዎ የD-CPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ከሆነ፣ DCPS ለእያንዳንዱ የአካል ጉድለት ላለበት ተማሪ የርቀት ትምህርት እቅድ በማዘጋጀት ታትሯል።

3) የእርስዎ ትምህርት ቤት የልጅዎን የትምህርት ደረጃ በትምህርት አመቱ መጀመርያ ላይ መፈተን እና እነዚያን ውጤቶች ለእርስዎ ማጋራት አለበት። ይህ ፈተና፣ "መረጃ ሰጭ ምዘና" ተብሎ የሚታወቀው፣ የልጅዎ ፍላጎቶች እንዴት እንደተቀየረ ትምህርት ቤቱ እንዲረዳ ይረዳዋል።

4) ትምህርት ቤትዎ ልጅዎን እንዲረዱ ሊረዳዎ ይገባል። ይህ ለርቀት ትምህርት ስልጠናን እና ግብዓቶችን ማቅረብን ያካትታል። እነሱ በተጨማሪ አዲስ ቴክኖሎጂን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል እርስዎን ማስተማር አለባቸው።

5) ትምህርት ቤትዎ በትምህርት ቤት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንቶች ላይ እነዚህን እርምጃዎች እንዴት እንደሚወስዱ ለእርስዎ መግለጽ አለባቸው። ትምህርት ቤትዎ "ቀጣይነት ያለው ትምህርት እና የትምህርት ቤት የማገገሚያ እቅድ" የሚል እቅድ አያዘጋጁ ነበር። ይህ እቅድ ከእርስዎ ጋር በቀጥታ ይጋራል። በተጨማሪ አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ፣የትምህርት ቤትዎ የኔትዎርክ ድረገጽ ላይ እና በOSSE ድረገጽ ውስጥ ይኖራል። ይህ እቅድ ሌሎች ነገሮችን ጨምሮ፣ ትምህርት ቤትዎ የሚከተሉትን እንዴት እንደሚያደርግ ያብራራል፣

- ተማሪዎችን ቤት ውስጥ እና በአካል ማስተማር
- በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን መከታተል
- ቤተሰቦችን ከሚያስፈልገው ቴክኖሎጂ ጋር ማገናኘት
- ለርቀት ትምህርት የአካዳሚክ፣ የባህርይ እና ልዩ ድጋፎችን እንደሚያካትት

ስለእነዚህ ግቦች የበለጠ ያንብቡ በ OSSE ቀጣይነት ያለው የትምህርት መርሀዎች እና የOSSE IDEA፣የFAPE አንቀጽ ክፍል B፣ የርቀት እና የድብልቅ ትምህርቶች ጋር የተያያዘ መመሪያ።

እዚህ የትምህርት ቤት የመገኛ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ፣

- DC የህዝብ ትምህርት
- DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች
- የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች

### 7 የኔ ልጅ በዚህ ጸደይ የትምህርት እድገቱን አጥቶ ይሆናል ብየ እሰጋለሁ። ልጄ እንዲተካከል ለማገዝ ትምህርት ቤቱ ምን ሊያደርግ ይችላል?

ለ2020-21 የትምህርት አመት፣ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች የ "ማገገሚያ አገልግሎቶችን" እያዘጋጁ ነው፣ ይህም ለልጅዎ የማገገሚያ አገልግሎቶች እቅዶችን ያካትታል። እነዚህ እቅዶች፣ በአጠቃላይ፣ ባለፈው

ጸደይ ያጡትን ትምህርት በተመለከተ ሊያግዙ ይችላሉ። ልጅዎ ከመደበኛው የትምህርት አመት ትምህርት ጎን ለጎን፣ የማገገሚያ አገልግሎቶችን ማግኘት አለባቸው።

ከማገገሚያ አገልግሎቶች በተጨማሪ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች የ"ማካካሻ አገልግሎቶች" ሊያስፈልጋቸው ይችላል። የማካካሻ አገልግሎቶቹ ትምህርት ቤት ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አገልግሎቶችን በማያቀርብበት ወቅት

ልጁ የሚያጣውን ትምህርት ለማካካስ የታቀዱ ናቸው። እነዚህ አገልግሎቶች ከ "ማገገሚያ አገልግሎቶች" በተጨማሪ ናቸው። የልጅዎ የIEP ቡድን፣ እራስዎን ጨምሮ፣ ልጅዎ የማካካሻ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ስለመሆኑ መወያየት አለበት።

## 8 ልጄ የህዝብ ባልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት ተመድቧል። የነሱ ትምህርት ቤት ስለበጋ ያላቸውን እቅድ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

የልጅዎ የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት ለዚህ የትምህርት አመት እቅዶችን ለማዘጋጀት ሪፈር ካደረጋቸው በDC ውስጥ ከሚገኘው የህዝብ ትምህርት ቤት ጋር እየሰሩ ነው። እነዚህ እቅዶች ትምህርት እንዴት እንደሚካሄድ ዝርዝሮችን ያካትታሉ -ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ቨርችዋል በሆነ መንገድ። እነሱ በተጨማሪ ትምህርት ቤቱ በአስተማማኝ ሁኔት እንዴት እንደሚሰራ ይገልጻሉ። ስለትምህርት ወይም የደህንነት እቅዶች ጥያቄዎች ካሎት፣ የልጅዎን የህዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ወይም የDC ትምህርት ቤትን ይጠይቁ።

በአጠቃላይ፣ እርስዎ ልጅዎ ስለሚማርበት የህዝብ ያልሆነ ትምህርት ቤት ስጋቶች ካሎት፣ ልጅዎን ሪፈር ያደረገውን በDC የሚገኘውን የህዝብ ትምህርት ቤት እና የልጅዎን ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድንን ማግኘት አለብዎ።
እዚህ ላይ የትምህርት ቤት ፕሮፋይሎችን፣ ከሚገኙበት አድራሻ ጋር ያገኛሉ፣

- የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች
- DC የህዝብ ትምህርት
- DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች

ለበለጠ መረጃ፣ የ OSSE የህዝብ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች መመርያን ይመልከቱ።

## ለእርዳታ ማንን ማግኘት እንደሚገባ

## 9 በትምህርት ቤት ውስጥ እኔ እና ልጄ ልናገኝ የሚገባን አገልግሎቶች እና ድጋፎችን አስመልክቶ እንዴት መከራከር እችላለሁ?

ልጅዎ የተመዘገበበት የDC ትምህርት ቤት ስለልጅዎ መከራከር የሚጀምሩበት የመጀመርያው ቦታ ነው። ስጋቶች ካሎት፣ ከልጅዎ የDC ትምህርት ቤት ጋር ማጋራት ይጀምሩ። እርስዎ የልጅዎን አስተማሪ፣ የልዩ ትምህርት አስተባባሪ ወይም ሌሎች የትምህርት ቤት ሀላፊዎችን ማግኘት ይችላሉ።

ስለዚህ ጉዳይ በስክል፣ በኢሜይል ወይም በቪድዮ ማውራት ይችላሉ። የሚከተሉት ሊረዱ የሚችሉ የግብዓቶች እና የደብዳቤዎች ናሙና ናቸው።

በDC ውስጥ ያሉ የተለያዩ ድርጅቶች እንዲከራከሩ ይረዳሉ። እነሱ በተጨማሪ ከትምህርት ቤትዎ ጋር ለመስራት ከተቸገሩ ስለሚኖሩት ቀጣይ እርምጃዎች ሊነግርዎ ይችላሉ። እነዚህ ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው፣

- የተማሪ ተሟጋች ቢሮ፣ የDC ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን በወላጅ ትምህርት፣ ማሰልጠን፣ ግብዓቶች እና ስልጠና ይረዳል።
- የእምባ ጠባቂ ቢሮ፣ በDC ውስጥ ስላሉ የህዝብ ትምህርት አስመልክቶ ወላጆች ያላቸውን ስጋቶች ለመርዳት ድርድርን እና ሽምግልናን የሚጠቀም ገለልተኛ ቢሮ።
- የፍትህ እና የትምህርት ተሟጋቾች (AJE)፣ የDC የወላጅ ስልጠና እና የመረጃ ማእከል። እነሱ ወላጆች ልጆቻቸውን ወክለው እንዲከራከሩ እና የወላጅ ስልጠና እና ግብዓቶችን በማቅረብ ይረዳሉ።

## 10 የልጄ ፍላጎቶች እንደተቀየሩ ወይም ትምህርታቸው ወይም ክህሎታቸው እንደቀነሰ ካመንኩ ማንን ማግኘት አለብኝ?

እርስዎ ስለልጅዎ ፍላጎቶች ስጋቶች ካሎት፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎታቸው እንዲመረመር ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለመጠየቅ ከአስተማሪያቸው ወይም የልዩ ትምህርት አስተባባሪው ጋር ያውሩ። ከልጅዎ ትምህርት ቤት ጋር ለመወያየት መዘጋጀት ይችላሉ በ፣

- ስለልጅዎ ትምህርት ያሎትን ሀሳቦች መጻፍ
- የልጅዎን አገልግሎቶች ዝርዝር ቤት ውስጥ መያዝ

የልጅዎ የIEP ቡድን ግምገማ የልጅዎን ፍላጎቶች "ዳግምግምገማ"ሊያስከትል ይችላል። ዳግም ምርመራ ማለት የልጁን የአካልጉዳተኝነት መደብን በድጋሚ በመወሰን ልጅዎ ከተለያዩ የልዩ ትምህርት ወይም አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማየት፣ የልጅዎን የአካዳሚክ አፈጻጸም እና ፍላጎቶች ለማየት የሚደረግ መደበኛ ሂደት ነው። የዳግም ግምገማ በየሶስት አመት ይደረጋል፣ ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ በተጨማሪ እርስዎ መጠየቅ ይችላሉ።

የOSSE የግልግል ዳኝነት ቢሮ ወይም የመንግስት የአቤቱታዎች ቢሮ ለሚከተሉት እርምጃዎች የሚኬድባቸው የመጀመርያ ስፍራዎች ናቸው፣ የግልግል ዳኝነት ቢሮ የወላጅ መምርያ ስለቀጣዩ እርምጃዎች የበለጠ መረጃ አለው።

## 11 እኔ እና ልጄ ከትምህርት ቤቱ የሚያስፈልገንን ድጋፍ ካላገኘን የት መሄድ እችላለሁ?

ከሞከሩ እና ከትምህርት ቤቱ ጋር ስለልዩ የትምህርት ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ ካልደረሳቹ፣ እርስዎ ሌሎች አማራጮች አሎት። ልጅዎ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ከሆነ፣ ድጋፍ ለመጠየቅ መጀመርያ የDCPS Office of Integrity ማግኘት ይችላሉ። ካልሆነ፣ የOSSE የግልግል ዳኝነት ቢሮ ወይም የመንግስት የአቤቱታዎች ቢሮ

ለሚከተሉት እርምጃዎች የሚኬድባቸው የመጀመርያ ስፍራዎች ናቸው፣

- የተሳለጠ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ፣ በገለልተኛ ሰው የሚመራ የIEP ቡድን ስብሰባ። ይህ ሊያስቡበት የሚገባ የመጀመርያው እርምጃ ሊሆን ይችላል። ልጅዎን በደምብ በሚያውቋቸው ሰዎች መካከል ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት እድል ይሰጥዎታል።
- ድርድር፣ በገለልተኛ ሶስተኛ ወገን የሚመራ ውይይት። ግቡ ትምህርት ቤቱ እና እርስዎ ስምምነት ላይ እንድትደርሱ ነው። ይህ በአብዛኛውን ጊዜ ከፍትሀዊ ሂደት ይፈጥናል።
- ፍትሀዊ የክርክር ሂደት፣ እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ ሁለታችሁም የየራሳቹን ክርክር በምስክሮች እና አስፈላጊ ሰነዶች በማቀረብ ለገለልተኛ አቤቱታ ሰሚ ባለሞያ ታቀርባላቹ። አቤቱታ ሰሚው ባለሞያ ውሳኔ ይሰጣል። በዚህ ላይ ይግባኝ ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።
- የመንግስት አቤቱታ፣ እርስዎ የጽሁፍ አቤቱታ ለOSSE ያቀርባሉ እና ህጉ መጣሱን ለማረጋገጥ ምርመራ ይደረጋል። የ

ግልግል ዳኝነት ቢሮ የወላጅ መምርያ የበለጠ መረጃ አለው።

## በዚህ አመት ልጅዎን እና ቤተሰብዎን መደገፍ

### 12 ልጄ ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እያገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቱን መጠየቅ ያለብኝ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?

የእርስዎ ትምህርት ቤት ለዚህ አዲስ የትምህርት አመት የአካል ጉድለት ያለባቸውን ተማሪዎች እንዴት መደገፍ እንደሚችል ሲያቅድ ነበር። የእርስዎ ትምህርት ቤት ትምህርት ቤት በተጀመረ በመጀመርያዎቹ ሁለት ሳምንቶች ልጅዎን የሚደገፉበትን እቅድ ማጋራት አለባቸው። እነሱ በተጨማሪ በድረገጻቸው ይህን መረጃ ማስቀመጥ አለባቸው።

የበለጠ ለማወቅ የልጅዎን አስተማሪ ወይም የልዩ ትምህርት አስተባባሪ ሊጠይቋቸው የሚችሉ ጥቂት ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፣

የመላው ትምህርት ቤት የዚህ አመት የትምህርት ቤት እቅዶች፣

- በዚህ ትምህርት ቤት ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጡ ድጋፎች እና አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? ለልጄ እና ለቤተሰቤ ተጨማሪ ድጋፎች ይኖራሉ?
- ቴክኖሎጂን እንዴት እየመረጣቹ ነው? ልጄ ሊጠቀመው እንደሚችል በምን መልኩ እያረጋገጣቹ ነው?
- ልጄ ከአስተማሪዎቹ ጋር በየቀኑ ምን ያክል ጊዜ ይኖረዋል?

የመማር ግቦች፣

- በልጄ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ የትኞቹ አገልግሎቶች አንላይን ይሆናሉ?
- የልጄ እድገት ቨርቹዋል በሆነ መንገድ እንዴት ይገመገማል? ይህ ምን ሊመስል ይችላል? እኔ ቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እችላለሁ?
- የትምህርት ቤቱ የጊዜ ሰሌዳ እና የግምገማ እቅድ ምንድን ነው፣ እና አስፈላጊ ሲሆን፣ የባህርይ ልዩነቶችን አይነት ተማሪ ተኮር በሆነ ምክንያት IEPዎችን የመከለስ እቅዳቸው ምንድን ነው?
- በዚህ ጸደይ ለልጄ ውጤታማ የሆነው እና ያልሆነው ምንድን ነው? ያንን መሰረት በማድረግ ምን አይነት ማስተካከያዎችን ማድረግ እንችላለን?

ለበለጠ ጥያቄዎች ትምህርት ቤትዎን መጠየቅ ይችላሉ፣ እዚህ ይመልከቱ፣

- በCOVID-19 ወቅት የአካል ጉድለቶች ያሉባቸው ተማሪዎች ወላጆች ከፍተኛ ጠቃሚ ምክሮች
- የመማር ጉድለት ላለባቸው ብሄራዊ ማእከል

እዚህ፣ የትምህርት ቤት ፕሮፋይሎችን ከሚገኙበት አድራሻ ጋር ማግኘት ይችላሉ፣

- DC የህዝብ ትምህርት
- DC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች
- የህዝብ ያልሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርት ቤቶች

### 13 ስለልጄ እድገት የት መማር እችላለሁ?

የልጅዎ ትምህርት ቤት ልጅዎ የልዩ ትምህርቱን እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ማግኘቱን የመቆጣጠር እና ለእርስዎ በየጊዜው የእድገት ሪፖርቶችን የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው። እነሱ አመቱን በሙሉ ይህን መረጃ ለእርስዎ ማቅረብ አለባቸው። በተለይም፣

- የትምህርት አመቱ በሚጀምርበት ወቅት፣ ትምህርት ቤትዎ የልጅዎን የትምህርት ደርጃዎች ማጣራት አለበት። እነሱ ይህን መረጃ ለእርስዎ ማጋራት አለባቸው፣ እና ይህን መረጃ የልጅዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ ማንኛውም ለውጦች እንዲኖር የሚያስገድድ መሆኑን ለማየት መጠቀም አለባቸው።
- በትምህርት አመቱ በሙሉ፣ የልጅዎ ትምህርት ቤት ከልጅዎ IEP እድገትን መከታተል አለባቸው። እነሱ ከእርስዎ ጋር በመደበኛ ሁኔታ ይገናኛሉ። ይህ የሚመሰረተው በልጅዎ IEP ላይ ባለው ግቦች ነው። የልጅዎን የIEP ለመረዳት እርዳታ ካስፈለጎት፣ የልጅዎን አስተማሪ ወይም ትምህርት ቤት ይጠይቁ።

ጥያቄዎች ካሎት፣ የልጅዎን አስተማሪ ወይም የልዩ ትምህርት አስተባባሪ መጠየቅ ይችላሉ።

ትምህርት ቤቶች በCOVID-19 የህዝብ ጤና አደጋ የርቀት ትምህርት ጊዜ የልጅዎን እድገት እንዲቆጣጠሩ ይጠበቅባቸዋል።

### 14 በዚህ የርቀት ትምህርት ወቅት ልጄን በተሻለ ሁኔታ ቤት ውስጥ እንዴት ልደግፈው እችላለሁ?

ለልጅዎ አስተማማኝ እና በፍቅር የተሞላ ቤት በመስጠት እና በትምህርት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ብዙ ነገር እያደረጉ ነው። በዚህ ጊዜ ልጅዎ ወይም ልጆችዎን ቤት ውስጥ መደገፍ ከአቅም በላይ ሆኖ ሊሰማዎ ይችላል፣ ነገር ግን የልጅዎ አስተማሪዎች ስለእናንተ ያስባሉ እና እርስዎን ለመደገፍ ከጎንዎ ናቸው።
ትምህርት ቤትዎ የልጅዎ የቤት ውስጥ ትምህርት እንዲያግዙ የሚያስችል ስልጠና እና ግብዓቶችን ሊያቀርብ ይገባል። የልጅዎን አስተማሪ ሁሉጊዜ እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።
የሚከተሉት ልጅዎን(ጆችዎን) በቤት ውስጥ ሊያግዟቸው የሚችሉባቸው የተወሰኑ ሀሳቦች ናቸው፣

- እነሱ የሚማሩበት ቦታ ያዘጋጁ። ቢቻል፣ ለመማሪያ ብቻ የሚሆን ቦታ ያዘጋጁ። የሀሳብ መበታተንን የሚገድብ እና የተደራጀ ቦታ ለማግኘት ይሞክሩ። ለተጨማሪ ጠቃሚ ምክሮች ቨርቹዋል ትምህርት ቤት የሚለውን ይመልከቱ።
- ቀና ቸውን ስርዓት እንዲያስይዙ ያግዟቸው። የርቀት ትምህርት በትምህርት ቤት ውስጥ ካለው ያነሰ ስርዓት አለው። ልጅዎ የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት እና አንድ ተግባር ላይ ለመቆየት እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ቢቻል፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊኖር ይችል እንደነበረው አይነት እለታዊ የጊዜ ሰሌዳ ይፍጠሩ።
  - የሚከተሉት ፖስተሮች፣ ህትመቶች እና ሌሎች ግብዓቶች ስርዓት ለመገንባት የሚያግዙ ናቸው።

- የቴሌቴራፒ እርዳታ። የቴሌቲራፒ ማለት በቨርቹዋል (ምናባዊ) የሚሰጥ ህክምና ማለት ነው። ልጅዎ ውጭ ካሉ ቴራፒስት ወይም ካውንስለር ጋር ቤት ውስጥ እየሰሩ ሊሆን ይችላል። ለቴሌቴራፒ የቤተሰብ ጠቃሚ ምክሮች አስፈላጊ ሲሆን የቪዲዮ ወይም የስልክ ጥሪዎችን ለማድረግ ዝግጁ መሆንን እና የልጅዎ ፊት ለአልግሎት አቅራቢ የሚታይ መሆኑን ማረጋገጥን ያካትታል።
- እራስዎን በሚገባ መንከባከብ። የራስዎን የአእምሮ ጤና መጠበቅ አስፈላጊ ነው። የAccess HelpLine ጋር በ1(888) 7WEHELP ወይም 1(888) 793-4357 በመደወል ማግኘት ይችላሉ።

ተጨማሪ ግብዓቶች፣

- ለቤት ውስጥ ትምህርት የቤተሰብ መምሪያ
- የአካል ጉድለት ላለባቸው ተማሪዎች የርቀት ትምህርት ግብዓቶች
- ተመራጭ የልዩ ትምህርት መተግበሪያዎች እና ድረገጾች
- ከባድ ወይም በርካታ የአካል ጉድለቶች ላሉባቸው ተማሪዎች የርቀት ትምህርት
- ልዩ ፍላጎት ያሏቸው ተማሪዎችን ከርቀት ትምህርት ጋር እንዲለማመዱ ማገዝ

## 15 በዚህ ወቅት ጭንቀትን ለመቋቋም እና ለደህንነት ቤተሰቤ ምን ማድረግ ይችላል?

ይህ በመላው DC ለሚገኙ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች አስጨናቂ ጊዜ እንደሆነ እናውቃለን። የሚያግዙ በርካታ ግብዓቶች አሉ።

ቨርቹዋል ስልጠና/ዎርክሾፕ ላይ መሳተፍ፣

- DCPS Parent University Online በDC ላሉ ሁሉም ቤተሰቦች የቨርቹዋል ዎርክሾፖች አለው። የወርክሾፑ የጊዜ ሰሌዳ እና ያለፉ ሪከርዶች ኦንላይን ይገኛሉ።
- እርስዎ እድሜው ከ6 አመት በታች የሆነ ልጅ የሚንከባከቡ ከሆነ፣ በአወንታዊ የአስተዳደግ ፕሮግራም ላይ ኦንላይን መሳተፍ ይችላሉ። ይህ ፕሮግራም በDC የባህርይ ጤና ዲፓርትመንት የሚቀርብ ነው። ይህ ፕሮግራም ፈታኝ የሆኑ ሁኔታዎችን መቋቋም እንዲለማመዱ ይረዳዎታል። ፕሮግራሙን ለማግኘት፣ አካውንት ሲፈጥሩ "dcparents"እንደ መግቢያ ቁልፍ ያስገቡ።

የድጋፍ ወይም ግብአቶች መኖር፣

- ከባህርይ ጤና ዲፓርትመንት ግብዓቶች፣
  - የDC Access HelpLine ጋር መደወል ይችላሉ በ1(888) 7WE-HELP ወይም 1(888)793-4357።
  - ይህ ባለ አንድ ገጽ የባህርይ ጤና በራሪ ጽሁፍ ያሉትን የድጋፍ አይነቶች ያብራራል።
  - የባህርይ ጤና ዲፓርትመንት የበለጠ መረጃ እና ግብዓቶች አሉት።
- የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት(CDC) ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን የሚያግዝ የግብዓት ገጽ አለው።
- ለልጅዎ ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ይፈልጋሉ? ከ"ባህርይ ጤና አስተባባሪ" ጋር ለመገናኘት ትምህርት ቤትዎ ጋር ይደውሉ እና ይጠይቁ። እነሱ ተማሪዎን ከአገልግሎቶች ጋር በማገናኘት ያግዛሉ።

ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ይገናኙ፣

- የመንግስት የልዩ ትምህርት የአማካሪ ፓነል (State Advisory Panel on Special Education, SAPSE) ሌሎች ቤተሰቦችን ሊያገኙበት የሚችሉ ስብሰባዎች አሏቸው።
- በDC የባህርይ ጤና ላይ የቤተሰብ እና የወጣቶች ተሳትፎ ኮሚቴ ቤተሰቦች ልምዶቻቸውን፣ ስጋታቸውን፣ እና ሀሳባቸውን የሚያጋሩበት ስፍራ ነው። ይህ ኮሚቴ በየወሩ ሶስተኛው አርብ ይገናኛል። ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ ለዶ/ር Chioma Oruh (ቺዮማ ኦሩህ) በ chioma@drchibornfree.com የቨርቹዋል የስብሰባ ሊንኩን ለማግኘት።
- የUnderstood.org የታሪክ ስብስብ የአካል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች COVID-19 እንዴት እየተቋቋሙ መሆኑን ያጋራል።

## ማጓጓዣ፣ የትምህርት ቤት ክትትል፣ስነምግባር፣የትምህርት ቤት ሪከርዶች

## 16 የትምህርት ቤት ህንጻዎች ከተከፈቱ፣ ልጄ አስተማማኝ የሆነ ትራንስፖርት ማግኘቱን እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?

የልጅዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ሊያካትት ይችላል። ጉዳዩ ይህ ከሆነ፣ የOSSE እና የአካባቢው ስፍራዎች የስራ አፈጻጸም ሁኔታን መሰረት በማድረግ የባስ ማጓጓዣ ወይም ክፍያን ሊሰጥ ይችላል።

ይህ በCOVID-19 የህዝብ ጤና አደጋ ወቅት ለተማሪዎች እና ሰራተኞች ደህንነት እና ጥበቃ ነው። ለማንኛውም ጥያቄዎች እርስዎ የOSSE የተማሪ ትራንስፖርት የወላጅ ግብአት ማእከል ክፍልን ማግኘት ይችላሉ በ (202) 576-5000 ወይም osse.dot@dc.gov

በCOVID-19 ወቅት ስለትራንስፖርት እና ደህንነት የበለጠ ለማንበብ፣ ከታች ያሉትን የግንኙነት መስመሮች ይጎብኙ፣

- ደረጃ 2 የትምህርት ቤቶች የጤና እና የደህንነት መመርያ
- COVID-19 DOT የፖሊሲ ማሻሻያዎች
- ለወላጆች፣ የአካል ጉድለት ላለባቸው ተማሪዎች ትራንስፖርት

## 17 ትምህርት ቨርቹዋል ከሆነ የትምህርት ቤት የመገኘት ክትትል እንዴት ይሰራል?

ትምህርት ቤቶች በዚህ አመት ትምህርት ላይ መገኘትን በየቀኑ ይቆጣጠራሉ። ትምህርት ቤትዎ የርቀት ትምህርትን የሚሰጥ ከሆነ፣ በትምህርት ላይ መገኘትን የሚከታተሉበት የተለያዩ አማራጮች አሏቸው። እነዚህ አማራጮች የሚያካትቱት፣

- ልጅዎ ቴክኖሎጂ ውስጥ ሲገባ መቆጣጠር
- አንድን የቤት ስራ ማስገባት
- ከአስተማሪው ጋር በስልክ ወይም በኢሜይል ግንኙነት ማድረግ።

የበለጠ ዝርዝር መረጃ በ OSSE የክትትል ፖሊሲ ሊገኝ ይችላል። ትምህርት ቤትዎ በትምህርት መገኘትን እንዴት እየተከታተለ መሆኑን አስመልክቶ ጥያቄዎች ካሉት፣ ትምህርት ቤትዎን ይጠይቁ። በተጨማሪ ልጅዎ በሰዓቱ ለመግባት የቴክኖሎጂ እርዳታ ካስፈለገው ትምህርት ቤትዎን ማግኘት አለብዎ።

## 18 የልጄ ትምህርት ቤት በዚህ አመት የስነምግባር አያያዙ እንዴት ነው?

ሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን ፖሊሲዎች እና የስነምግባር ደምብ መከተል አለባቸው። ይህ ተገቢ የሆነ የትምህርት ቤት ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የመሳሰሉ ነገሮችን ያካትታል። ነገር ግን፣ ልጅዎ የስነምግባር ቅጣት ከመጣሉ በፊት ተጨማሪ እርምጃዎችን ትምህርት ቤቱ እንዲወስድ የሚጠይቅ፣ የፌደራል ልዩ የትምህርት ህግ በሆነው በIDEA ስር ልዩ ጥበቃዎች አላቸው። ስለእነዚህ መብቶች የበለጠ ለመማር፣ የትምህርት ቤት ውስጥ ስነምግባር የሚለውን አጭር ቪድዮ ይመልከቱ። እነዚህ መብቶች በርቀት ትምህርት ወቅትም የተጠበቁ ናቸው።

ትምህርት ቤትዎ የርቀት ትምህርትን በሚያሰላስልበት ወቅት በዚህ አመት የስነምግባር ፖሊሲውን ሊያሻሽል ይችላል። ትምህርት ቤትዎ ይህን የተሻሻለውን ፖሊሲ በድረገጻቸው ላይ በቀላሉ እንዲገኝ ማድረግ አለባቸው። ፖሊሲው ልጅዎ የትምህርት ቤቶቹን ህጎች የማይከተል ከሆነ የሚፈጠረውን ያብራራል።

ለተጨማሪ መረጃ፣

- የትምህርት ቤት ስነምግባር፣ ከIEPs እና 504 እቅዶች ጋር የተማሪዎች መብቶች

## 19 የልጄን የትምህርት ቤት ወይም የልዩ ትምህርት ሪከርዶች ቅጂን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የልጅዎን ሪከርዶች ቅጂ ከነሱ ትምህርት ቤት መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ልዩ የትምህርት ሪከርዶችን ያካትታል።

- ልጅዎ የColumbia (ኮሎምቢያ) ግዛት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools, DCPS) አካል የሆነ ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ (ወይም አሁን የተዘጋ የDCPS ትምህርት ቤት የተማረ ከሆነ)፣ ሪከርዶቹን ከDCPS ይጠይቁ።
- ልጅዎ የDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ፣ ሪከርዶቹን ከDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ይጠይቁ ።
- ልጅዎ አሁን የተዘጋ የDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ከተማረ፣ ይደውሉ (202) 328-2660 ወይም ኢሜይል ያድርጉ dcpublic@dcpcsb.org።
- ልጅዎ የህዝብ ያልሆነ ልዩ ትምህርት ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ፣ ልጅዎን ሪፈር ካደረገ የህዝብ የDC ትምህርት ቤት ሪከርዶቹን መጠየቅ አለብዎ። ለእርስዎ ተፈጻሚ የሆነው አማራጭ ለመምረጥ ከላይ ያሉትን ምድቦች ይጠቀሙ።

የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ወይም ከላይ ባለው ላይ ችግር ካጋጠሞት፣ የበለጠ መማር ይችላሉ ወይም የOSSE ድረገጽን የተማሪ ሪከርዶችን ማግኘት ይጎብኙ።